**የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን**

**4ኛ ዓመት 1ኛ መደበኛ ጉባዔ**

መስከረም 29 ቀን 2011 ዓ.ም

አመልካች፡- ወ/ሮ ቦጋለች አሰፋ

ተጠሪ፡- አቶ ስሜ ነጋሽ

**የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት አመልካች ያቀረቡትን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡**

**ውሳኔ**

ጉዳዩ የተጀመረው አመልካችና ተጠሪ በጋብቻ አብረው ከቆዩ በኋላ ጋብቻቸው በፍቺ ስለፈረሰ የአሁን አመልካች የንብረት ክፍፍል ጥያቄን ለሲናና ወረዳ ፍ/ቤት በማቅረባቸው ሲሆን ለዚህ አቤቱታ መነሻ የሆነው በሮቤ ከተማ በደንሳ ጨፌ ቀበሌ ውስጥ 200 ካ.ሜ ቦታ ላይ የሚገኝ ቤት በ10/11/2003 ዓ.ም በተደረገው የጋብቻ ውል የጋራ ንብረት እንዲሆን የተዋዋልን ስለሆነ ተጠሪ ሊያካፍሉኝ ይገባል በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪም ቀርበው ንብረቱን ከጋብቻ በፊት ያፈራሁት ስለሆነ አመልካች መብት የላቸውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ግራቀኙን ካከራረከ በኋላ ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ቤት ከጋብቻ በፊት ተጠሪ ያፈሩት ቢሆንም ተጠሪ የጋብቻቸው ስነ-ስርዓት በተፈፀመበት ቀን ማለትም በ10/11/2003 ዓ.ም አሁን ክርክር ያስነሳውን ቤት የጋራቸው እንዲሆን ተስማምተው የፈረሙ መሆኑን በቀረቡት የሰውና የፅሁፍ ማስረጃ አረጋግጫለሁ በማለት ቤቱ የጋራቸው ስለሆነ እኩል ይካፈሉ ሲል ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪም ለባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትና ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ደቡብ ቋሚ ችሎት በየደረጃው ይግባኝ ቢጠይቁም የወረዳውን ፍ/ቤት ውሳኔ አፅንቷል፡፡ ተጠሪ በውሳኔው ቅር በመሰኘት ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ሰበር ሰሚ ችሎቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ክርክር ያስነሳው ቤት የተሰራው በ1996 ዓ.ም ሲሆን አመልካችና ተጠሪ በ9/12/2000 ዓ.ም መሆኑን ከማዘጋጃ ቤት የቀረበው ማስረጃ ያስረዳል፣ ተጠሪና አመልካች ንብረታቸውን በተመለከተ ስምምነት ያደረጉት በ10/11/2003 ዓ.ም ጋብቻው ከተፈፀመ ከሁለት ዓመት በኋላ ሲሆን ይህ ውል ፍ/ቤት ቀርቦ ስለመመዝገቡ የቀረበ ማስረጃ የለም፣ የኦሮሚያ የቤተሰብ ሕግ አንቀፅ 89 ባልና ሚስት በጋብቻ ውስጥ በንብረት ላይ የሚያደርጉት የውል ስምምነት ፍ/ቤት ቀርቦ ካልተመዘገበ ተቀባይነት እንደሌለው ይገልፃል በማለት ክርክር ያስነሳው ቤት የተጠሪ የግል ንብረት ስለሆነ አመልካች ሊካፈሉ አይገባም ሲል የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

አመልካች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታቸውን ቢያቀርቡም የተፈፀመ የሕግ ስህተት የለም በማለት መዝገቡን የዘጋው መሆኑን በመጥቀስ የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጥላቸው ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

ጉባኤውም የቀረበውን አቤቱታና የተሰጠውን ውሳኔ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጭብጦች በመያዝ ጉዳዩን መርምሮታል፡፡ በጭብጥነት የያዘው የመጀመሪያው ጉዳይ የጋብቻ ውሉ የተፈፀመውና ጋብቻ ስነ-ስርዓት የተደረገው በተመሳሳይ ቀን ነው ወይስ ጋብቻ ከተፈፀመ በኋላ ነው? የሚል ሲሆን ሁለተኛው ጭብጥ ደግሞ ውሉ በሁለቱ ወገን መኖሩን ተጠሪ አለመካዱ ውጤቱን ያስቀይረዋል አያስቀይረውም? የሚለው ጭብጥ መልስ ማግኘት የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ አሁን ክርክር ያስነሳው ቤት ተጠሪ ከጋብቻ በፊት በ1996 ዓ.ም በግላቸው መስራታቸው አልተካደም፡፡ አመልካች እና ተጠሪ በማዘጋጃ ቤት በቀን 09/12/2000 ዓ.ም ጋብቻ ለመፈፀም መፈራረማቸውን የሚገልፁ ሰነድ የቀረበ ሲሆን ተጠሪ ይህ በማዘጋጃ ቤት የተደረገው የፊርማ ቀን የጋብቻ ሥነ ሥርዓት የተደረገበት ቀን ነው በማለት ሲከራከሩ አመልካች ደግሞ ይህ ቀን የፍጥምጥም (ቀለበት) ቀን ነው እንጂ የጋብቻ ቀን አይደለም፣ ጋብቻ የፈፀምነው በ10/11/2003 ሆኖ ውሉን የተፈራረምነው በዚሁ ቀን ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

በሁለቱም ጊዜ የተፈረሙ የፅሁፍ ማስረጃዎች የቀረቡ ሲሆን በተለይ በስር ፍ/ቤት በአመልካች በኩል የቀረቡት የሰው ምስክሮች አመልካች እና ተጠሪ በ10/11/2003 ዓ.ም የጋብቻ ሥነ ሥርዓታቸውን የፈጸሙ መሆኑንና ተጠሪ በዚሁ ቀን አሁን ክርክር ያስነሳውን ቤት የጋራ መተዳደሪያችን ነው ብለው በፍቃዳቸው ተስማምተው ውል መፈረማቸውን እንዲሁም ምስክሮቹም በሥነ ስርዓቱ ላይ የነበሩ መሆኑን ገልፀው መስክረዋል፡፡ የጋብቻ ውሉና የሰው ምስክሮች ቃል ተደምረው የአመልካች እና የተጠሪ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት የተፈጸመው በ10/11/2003 ዓ.ም መሆኑን እና የጋብቻ ውሉም የተፈረመው በዚሁ ዕለት በሰርገኞች ፊት መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ የኦሮሚያ የቤተሰብ ሕግ ባልና ሚስት ንብረታቸውን በተመለከተ ከጋብቻ በፊት የአንዱ የነበረውን ሀብት የጋራ እንዲሆን መዋዋል እንደሚችሉ ፈቅዶ ከጋብቻ ቀን በኋላ የሚደረግ የንብረት ውል በፍርድ ቤት መመዝገብ እንዳለበት በአንቀጽ 89 ላይ ደንግጎ ይገኛል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ላይ ባልና ሚስት የሰርግ ሥነ ሥርዓታቸውን በፈጸሙበት ቀን ተጠሪ በሰርገኞች ፊት በራሳቸው ፍቃድ ቤቱ የጋራቸው እንዲሆን ውል ገብተው መፈረማቸውን የቀረቡት ምስክሮች ያረጋገጡ መሆኑን፣ በሌላ በኩል ተጠሪ ውሉን አላደረኩም ብለው አለመከራከራቸውን፣ ጋብቻ ከመፍረሱ በፊት ውሉ እንዲፈርስ የቀረበ ጥያቄ አለመኖሩን፣ ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች አሁን ክርክር ካስነሳው ቤት ላይ የባለቤትነት መብት ያላቸው መሆኑን፣ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች እና ተጠሪ የተጋቡት በቀን 09/12/2000 ዓ.ም ነው የሚል ግምት በመውሰድ የጋብቻ ውሉ ጋብቻ ከተፈጸመ ከሁለት አመት በኋላ ስለሆነ የኦሮሚያ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 89 ባልና ሚስት በጋብቻ ውስጥ በንብረት ላይ የሚያደርጉት የውል ስምምነት ፍ/ቤት ቀርቦ ካልተመዘገበ ተቀባይነት እንደሌለው ስለሚገልጽ ውሉ ተቀባይነት የለውም፤ አመልካች ቤቱን ሊካፈሉ አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ የአመልካችን የንብረት ባለቤትነት መብት ያሳጣ ውሳኔ ስለሆነ ውሳኔው ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀጽ 1 የንብረት ባለቤትነት መብት ጋር የሚቃረን ስለሆነ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል

በማለት ጉባኤው የውሳኔ ሃሳቡን በሙሉ ድምፅ ተስማምቶ ለመጨረሻ ውሳኔ ለምክር ቤቱ አቅርቧል፡፡

ከዚህም በመነሳት ምክር ቤቱ በሕገ መንግስት ትርጉም እና የማንነት ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ጉዳይ ታይቶ እንዲቀርብ መርቶት የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ባቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ላይ ሰፊ ውይይት ካደረገ በኋላ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 79 ንዑስ አንቀፅ 1 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ጉዳዩን በመመርመር ባልና ሚስቱ የተጋቡት በቀን 09/12/2000 ዓ.ም መሆኑን ግምት በመውሰድ ሳይሆን ከመዘጋጃ ቤቱ የቀረበውን የጽሁፍ ማስረጃ መሠረት በማድረግ እና ውል የተደረገው ጋብቻ ከተፈፀመ በኋላ በቀን 10/11/2003 ዓ.ም መሆኑን ከቀረቡት የጽሁፍ ማስረጃዎች በማረጋገጥ በኦሮሚያ የቤተሰብ ሕግ አንቀፅ 89 ላይ “ባልና ሚስት በጋብቻ ውስጥ በንብረት ላይ የሚያደርጉት የውል ስምምነት ፍርድ ቤት ቀርቦ ካልተመዘገበ ተቀባይነት የለውም” ተብሎ የተደነገገውን መሠረት በማድረግ በስር ፍ/ቤቶች የተፈፀመውን የሕግ ስህተት በማስተካከል ውሳኔውን መሻሩና ይኸው ውሳኔ በፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት መፅናቱ በቤተሰብ ሕጉ መሰረት በመሆኑ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ምክር ቤቱ ወስኗል፡፡

## <u>ትዕዛዝ</u>

1. የውሳኔው ግልባጭ ለባለጉዳዩ ይሰጥ፡፡
2. የምክር ቤቱን ውሳኔ እንዲያውቁት ለፌደራል ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ይላክ፡፡

የሰ/መ/ቁ 127459

መስከረም 23 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዳኜ መላኩ
ረታ ቶሎሳ
ተኽሊት ይመሰል
ቀነአ ቂጣታ
አብዱ ካሳሁን

አመልካች፡- ጣና የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮና ኢንዱስትሪ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር
- ጠበቃ ሚሊዮን አሰፋ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የድሬዳዋ አስተዳደር ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን - ዐ/ሕግ አብይ ታደሰ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 117051 የካቲት 22 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ሊታረምልኝ ይገባል በማለት አመልካች ሚያዚያ 26 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ 06 ገጽ የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የአስተዳደር መስሪያ ቤት ውሎች በአድጁዲኬሽን የሙግት መፍቻ ዘዴ መዳኘት የሚችሉ መሆን አለመሆናቸውን የሚመለከት ነው፡፡ ለጉዳዩ መነሻ ምክንያት የሆነው አመልካች ለተጠሪ 12 ውሃ ጉድጓድና 2 የውሃ ጉድጓድ መቆጣጠሪያ ለመገንባት፤ ተጠሪ ደግሞ ብር 59,922,705 /ሃምሳ ዘጠኝ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሃያ ሁለት ሺህ ሰባት መቶ አምስት ብር/ ለመክፈል ስምምነትአድርገው እንደነበር በማግለፅ በተጠሪ ጥፋት የተነሳ ሥራው በስምምነቱ መሠረት ሊፈፀም ባለመቻሉ የውል ጊዜው ለተጨማሪ ስድስት ወራት እንዲራዘም፤ የዋጋ ለውጥ እንዲደረግ፤ ካሳና ወለድ ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍል በመጠየቅ የቀረበ ክስ ነበር፡፡

ተጠሪም በበኩላቸው ጥፋት አለመኖሩን፤ችግሩ የተፈጠረው በአመልካች የቴክኒክ ብቃት ችግር መሆኑን በመጥቀስ የካሳ ክፍያም ሆነ የጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄው ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ክሱ ውድቅ እንዲሆን መልስ አቅርቧል፡፡

ግራቀኙ ወገኖች አስቀድሞ ባደረጉት ውል አንቀጽ 24 መሠረት በአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት የተመደበው አድጁዲኬተር ጉዳዩን እንዲዳኝ ተደርጎ በሰጠው ውሳኔ ስለጉዳዩ ተገቢውን ማጣራት ሲያደርግ ቆይቶ አመልካች በጠየቁት መሠረት የሥራ ማጠናቀቂያ ጊዜ በስድስት ወራት እንዲራዘም፤ተጠሪ ቅድመ ክፍያ ሳዘገየበት ወለድ እንዲከፍሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪው በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባቀረበው ይግባኝ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው ውል የአስተዳደር መስሪያ ቤት ውል መሆኑን ጠቅሶ የአስተዳደር መስሪያ ቤት ውሎችን ሚመለከቱ አለመግባባቶች የግልግል አካል ዳኝነት መስጠት እንዳይችል በህግ ክልከላ የተደረገ በመሆኑ በተያዘው ጉዳይ አድጁድኬተር ጉዳዩን ያየው ስልጣን ሳይኖረው ነው የሚልና ሌሎች ዝርዝር የቅሬታ ነጥቦችን በማቅረባቸው

ፍርድ ቤቱ ቅሬታው መልስ ሰጭን ያስቀርባል በማለት ግራ ቀኙን አከራክሮ ሲያበቃ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው ውል የአስተዳደር ውል ነው፡፡ የአስተዳደር ውሎች በግልግል ዳኝነት ሊታዩ የማይገባቸው ለመሆናቸው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 315(2) ደንግጓል፡፡ ስለሆነም አድጁዲኬተር ጉዳዩን ያየው በህግ በተከለከለ ጉዳይ ላይ በተደረገው ውል መነሻነት በመሆኑ ሥልጣን ሳይኖረው ነው በማለት የአድጁዲኬተሩን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንን ዳኝነት ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበው የሥር ፍርድ ቤቶች ዳኝነት መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል በሚል ሲሆን አቤቱታው በአጭሩ፡- አድጁዲኬሽን በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ዓለም አለመግባባቶችን ለመፍታት ጠቃሚ የሆነና ከግልግል ዳኝነት የተለየ የአለመግባባት መፍቻ መንገድ ሆኖ እያለ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትአድጁዲኬሽንን ከግልግል ዳኝነት ጋር በማመሳሰል የተያዘውን ጉዳይ አድጁዲኬተር ማየት አይችልም በማለት መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ውሳኔ ነው የሚሉና ሌሎችንም የቅሬታ ነጥቦች አጠቃሎ የያዘ ነው፡፡

ሰበር አጣሪ ችሎቱም መዝገቡን መርምሮ በግራቀኙ ተከራካሪዎች መካከል የተፈጠረው አለመግባባት በውላቸው አንቀጽ 24 መሠረት በአድጁዲኬተር መታየቱ ያላግባብ ነው ተብሎ የተወሰነበትን አግባብ ለማጣራት አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል በማለቱ ተጠሪ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ክርክሩ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ተጠናቋል፡፡ እኛም አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አንጻር ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም አድጁዲኬተር (ገላጋይ ዳኛ) የአስተዳደር ውልን በተመለከተ የሚነሱ ክርክሮችን ለመዳኘት ይችላል ወይስ አይችልም? የሚለው ጭብጥ ምላሽ ማግኘት ያለበት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ከመዝገብ ምርመራው መገንዘብ እንደተቻለው በአመልካችና በተጠሪ መካከል እ.አ.አ አፕሪል 06 ቀን 2013 የተደረገ ውል ለመኖሩ በግራቀኙ ወገኖች የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ በዚሁ ውል አንቀጽ 24 ሥር አለመግባባቶች የሚፈቱበትን አግባብ በተመለከተ አስቀድሞ በአድጁዲኬተር ወይም በገላጋይ ዳኛ ሊታይ እንደሚገባው፤ይህ ገላጋይ ዳኛም በአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ሊመደብ የሚገባው መሆኑን እንዲሁም በገላጋይ ዳኛው ውሳኔ የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት ምን ሊሆን እንደሚገባ ጭምር ስምምነት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ ለህዝብ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ሲሆን ለክርክሩ መነሻ የሆነው የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮም ለህዝብ ጥቅም ለመስጠጥ የታሰበ በመሆኑ ውሉ ለህዝብ ጥቅም የተደረገ ውል መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 3132(ለ) ሥር እንደተመለከተው ከህዝብ አግልግሎት ሥራ ጋር የተያያዙና ለውሉ አፈፃፀምም የተዋዋዩን የድሬዳዋ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ያልተቋረጠ ተካፋይነት የሚጠይቅ በመሆኑ ውሉ የአስተዳደር መስሪያ ቤት ውል ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪው ከአመልካች ጋር ያደረጉት ውል አስተዳደር መስሪያ ቤት ውል ነው መባሉ የሚነቀፍበት መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 315(2) ሥር በግልፅ እንደተመለከተው የአስተዳደር መስሪያ ቤት ውሎችን በግልግል ዳኝነት እንዳይታዩ ህግ ክልከላ አድርጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አለመግባባትን ለመዳኘት በውል ሥልጣን የተሰጠው አድጁዲኬተር ወይም ገላጋይ ዳኛ ሲሆን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉ አንቀጽ 315(2) የአስተዳደር ውልን አስመልክቶ የሚነሳ

አለመግባባትን ለመዳኘት የማይችለው የግልግል ዳኝነት አካል ወይም አርቢትሬተር ነው፡፡ እዚህ ላይ ሊነሳ የሚገባው ዋናው ነጥብ የአድጁዲኬተር እና የአርቢትሬተር አንድነትና ልዩነታቸው ምንድን ነው አርቢትሬተር የአስተዳደር ውሎችን እንዳይዳኝ በህግ ክልከላ ከተደረገበት ዓላማ አንፃር አድጁዲኬተር የአስተዳደር ውሎችን እንዲዳኝ ሊፈቀድለት ይገባል ወይ? ከዚህ አንፃር አመልካችና ተጠሪ ስለአለመግባባት አፈታት በውላቸው አንቀጽ 24 ያደረጉት ስምምነት በህግ ተቀባይነት ያለው ነው ማለት ይቻላል ወይ? የሚሉት ነጥቦች ናቸው፡፡

በመሠረቱ አለመግባባቶችን ለመፍታት ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ውጭ የሆኑ የተለያዩ አማራጭ የሙግት መፍቻ ሥርዓቶች እንዳሉ የሚታወቅ ነው፡፡ ከእነዚህ አማራጭ የሙግት መፍቻ ስልቶች ውስጥ በአገራችን የሥነ ሥርዓት ህግ ዕውቅና ያገኙት ድርድር፤እርቅ፤ግልግል እና ስምምነት ሲሆኑ አድጁዲኬሽ ወይም ጉዳዩን በገላጋይ ዳኛ የመፍታት አሰራር በብዙ የዓለም ሀገሮች የሚሰራበት ከመሆኑም በላይ በንግዱ ህብረተሰብ መካከል የሚፈጠረውን አለመግባባት ለመፍታት በአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በኩል ደንብ ወጥቶለት እየተሰራበት ይገኛል፡፡

አለመግባባት የተፈጠረበትን ጉዳይ መርምሮ ውሳኔ የመስጠት ሂደት አድጁዲኬሽን እንደሚባል የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ባወጣው ደንብ አንቀጽ 2 ሥር የተመለከተ ሲሆን ግልግል በግራቀኙ ወገኖች መካከል የሚፈፀም ውል ሲሆን ውሉን መሠረት በማድረግ የግልግል ዳኛ የሚሰጠው ውሳኔ አስገዳጅ ውጤት እንዳለው ከፍትሐብሔር ህግ አንቀጽ 3325 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ነው፡፡ ስለ

ሁለቱ የሙግት መፍቻ ሥርዓቶች አንድነት ስንመለከት ውሳኔው አስገዳጅነት ያለው መሆኑ እና ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ውጭ በሆነ ሁኔታ አለመግባባት የሚፈታባቸው መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡አለመግባባት የተፈጠረበትን ጉዳይ መርምሮ ውሳኔ የመስጠት ሂደት አድጁዲኬሽን እንደሚባል የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ባወጣው ደንብ አንቀጽ 2 ሥር የተመለከተ ሲሆን ግልግል በግራቀኙ ወገኖች መካከል የሚፈፀም ውል ሲሆን ውሉን መሠረት በማድረግ የግልግል ዳኛ የሚሰጠው ውሳኔ አስገዳጅ ውጤት እንዳለው

ከፍትሐብሔር ህግ አንቀጽ 3325 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ነው፡፡ ስለ ሁለቱ የሙግት መፍቻ ሥርዓቶች አንድነት ስንመለከት ውሳኔው አስገዳጅነት ያለው መሆኑ እና ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ውጭ በሆነ ሁኔታ አለመግባባት የሚፈታባቸው መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/አንቀጽ 315(2) ድንጋጌ በግልግል የዳኝነት ሥርዓት የአስተዳደር መስሪያ ቤት ውሎች ሊዳኙ እንደማይገባ የደነገገበት አግባብ ፍትህ ከአማራጭ የሙግት መፍቻ የሚገኝ መሆኑን በመዘንጋት ሳይሆን የአስተዳደር ውሎች ጉዳይ የህግ የበላይነትን መርህ በአደረገው መደበኛ ፍርድ ቤት መታየቱ በውሎቹ ሊደረስበት የታሰበውን ዓላማ ለማሳካት እንደሚያስችል ታምኖበት የተወሰደ የመንግስት ፖሊሲ አማራጭ እንደሆነ መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡ አማራጭ የሙግት መፍቻ መንገዶች የራሳቸው የሆነ ጠቀሜታ ያላቸው የመሆኑን ያህል የጎንዮሽ ጉዳትም ሊኖራቸው እንደሚችል መገንዘብ ይገባል፡፡ በተለይም በአገራችን ሥርዓት ተበጅቶላቸው በጠነከረ አኳኋን የሚመሩ የመንግስትንና ህዝብን ጥቅም ሊያስጠብቁ የሚችሉ የተሟላ ኃላፊነትና ተጠያቂነት የተሰጣቸው አማራጭ ሙግት መፍቻ ተቋማት

ከአለመጠናከራቸው አንፃር የአስተዳደር ውሎች በግልግል ዳኝነት አካል እንዳይታዩ ህግ አውጭው አካል ለመምረጡ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/አንቀጽ 315 ይዘት መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡

የአስተዳደር መስሪያ ቤት ውሎች በግልግል ዳኝነት ሊታዩ የማይገቡ ስለመሆኑ በህግ ከተመለከተና ዓላማውም የህግ የበላይነትን ለማስከበር ህግ አውጭው ለአስተዳደር ውሎች ዳኝነት የመረጠው ስለመሆኑ ግንዛቤ ከተወሰደ አድጁዲኬተር ማለትም የአርቢትሬተር ዓይነት አስገዳጅ ውሳኔ የሚሰጥ አካል የአስተዳደር ውሎችን እንዲዳኝ የሚያስችሉ ስምምነቶች የህግ ውጤታቸው ምን ይሆናል? የሚለውን ጥያቄ ምላሽ መስጠት ይጠይቃል፡፡ አርቢትሬተር የአስተዳደር ውሎችን በተመለከተ መዳኘትየማይችል ከሆነ አድጁዲኬተር ከሚሰጠው የዳኝነት ባህሪ አንፃር የአስተዳደር ውሎችንሊዳኝ የሚችል አይሆንም፡፡ ምክንያቱም አድጁዲኬተርም ሆነ አርቢትሬተር አስገዳጅ ውሳኔ የሚሰጡ አማራጭ የሙግት መፍቻ አካላት ስለሆኑ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አድጁዲኬተር ከአርቢትሬተር የተለየ አማራጭ የሙግትመፍቻ ተቋም ተደርጎ ሊወሰድ ስለማይችል የሥር ፍርድ ቤቱ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገ ውል የአስተዳደር መስሪያ ቤት ውል በመሆኑ በገላጋይ ዳኛ እንዲታይህጉ አይፈቅድም ሲል የደረሰበት ድምዳሜ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 315(2)ን፣የፍትሐ ብሔር ህጉን አንቀጽ 1678(ለ) 3131፣3132(ለ) ያገናዘበ በመሆኑ የሚነቀፍበት መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተገኘም፡፡ለማጠቃለል ለሰበር አቤቱታው መቅረብ ምክንያት የሆነውን ዳኝነት የሰጠው ገላጋይ

ዳኛ በተያዘው ጉዳይ ላይ የመወሰን ስልጣን የሌለው ነው፡፡ ገላጋይ ዳኛ ሥልጣን አልነበረውም የሚል ድምዳሜ ላይ ከተደረሰ በአመልካች በኩል የሚቀርቡ ሌሎች የቅሬታ ነጥቦችን በጭብጥነት ይዞ መወሰን ተገቢ አይሆንም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 117051 የካቲት 22 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. የአስተዳደር መስሪያ ቤት ውሎችን አስመልክቶ የሚነሳ አለመግባባትን አይቶ ለመወሰን ገላጋይ ዳኛ (Adjudicator) ሥልጣን የለውም በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ክርክር ለወጣ ወጭና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት